# ምንተኑ አአስየኪ

ምንተኑ አአስየኪ እሴተ
በእንተ ኩሉ ዘከበርኪ ሊተ

የቅዱሳን ተስፋ የትንቢት ምዕራፍ
የስደተኞች ስንቅ የምህረት ደጃፍ
የፍጥረት መመኪያ ምክንያተ ድኂን
ለእኔም ለመንገዴ ስለሆንሽኝ ብርሃን
አዝ...

የዓለም ኑሮ ማርኮኝ ልቤ ሲዋልል
በፈተናው ብዛት በህይወት ስዝል
ለሥጋዬ ፈቃድ ከቶ ስላልተውሽኝ
ለነፍሴም ሠላምን ስላስገኘሽልኝ
አዝ...

በኃጢአት መጕስቆሌን ደካሜን ሳታይ
በኃዘን በችግሬ ከእኔ ሳትለይ
ከመከራዬ አዘቅት በአንቺ ስለወጣሁ
ለብዙ ውለታሽ ምን እከፍልሻለሁ
አዝ...